


የፖለቲካ ፕሮግራም

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር
(ኢብአግ)

# ማውጫ


መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

ክፍል 1፤ የፖለቲካ ዓላማ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

ክፍል 2፤ የፖለቲካ ስልት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

ክፍል 3፤ ፖለቲካዊ ጉዳዮች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6

ክፍል 4፤ የኢኮኖሚ ጉዳዮች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 7

ክፍል 5፤ ማህበራዊ ጉዳዮች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8

5.1፤ ትምህርት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8

5.2፤ ጤና . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 9

5.3፤ ሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች . . . . . . . . . . . . . . . . . 10

5.4 ሃይማኖት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 11

5.5 ቋንቋ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 11

ክፍል 6፤ የዜጎች መሠረታዊ መብቶች . . . . . . . . . . . . . . . . 12

ክፍል 7፤ የሀገር መከላከያ የፖሊስና የብሔራዊ ደህንነት አደረጃጀት . . 13

7.1 የሀገር መከላከያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 13

7.2 ፖሊስና ደህንነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 13

ክፍል 8፤ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 14

# መግቢያ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር (ኢብአግ) በዚህ ወቅት ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊያን  የሚያስፈልገውን የፖለቲካ መስዋዕትነት ለመክፈል በቆራጥ ልጆቿ ተመስርቷል።

ዛሬ ኢትዮጵያ በዘመናችን ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ እጅግ ተራቁታና ተጎሳቁላ ትገኛለች። በዚህም ምክንያት ተቆርቋሪ ልጇቿ ጥበብን በመመርኮዝና ፈጣሪ አምላካችንን በመተማመን የሕዝቧን ጭቆና ለማስወገድና ዘለቄታዊ መፍትሄና ብልጽግናን ለማስፈን ታጥቀን ተነስተናል።

የህወሃት/ኢህአዴግ ዘረኛና ጎጠኛ መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ “የሚበጅህን እናውቅልሃለን” በማለት በጎሳ በመለያየት፥ የሀገሪቱን ንብረት በመበዝበዝ፥ ለሃቅ የቆሙ ልጆቿን በማደን፥ በማሰርና በመግደል እና የሀገሪቱንም ድንበር በመሸጥ በጠቅላላው በህገ ወጥ አገዛዝ ከባድ ጭቆና እየፈጸመ ይገኛል። ህወሃት/ኢህአዴግ ህዝቡን ከገዛ ሀገሩ ከሥራውና ከመኖሪያ ሥፍራው አፈናቀሉት፤ የሚናገርበትን ቋንቋና የሚኖርበትን ክልል ወሰኑለት፤ በሃገርና በህዝብ ላይ የጥላቻና የልዩነት መንፈስ ዘሩ። ህወሃት/ኢህአዴግ የሀገሪቱን ህልውና፥ የሕዝቡን አንድነትና ታሪክ ክዷል፤ የነጻነትና የህልውና ምልክት የሆነውን ሰንደቅ ዓልማችንን አዋርዷል፤ ቀድዷል፤  አራክሷልም።

የዚህ ዓይነት የፖለቲካ አመለካከት ተወግዶ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክና ወግ የብሄራዊ የረዥም ዘመን አብሮ የመኖር ባህሉንና ፍላጎቱን መሠረት ያደረገ ሃገር በቀልና ማህበራዊ መዋቅሮችን ከታሪክና ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ያዛመደ፥ ከባዕዳን ተፅዕኖና ጣልቃ ገብነት ነፃ የሆነ፥ የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስከብር ማህበራዊ ሥርዓት መመስረት ያስፈልጋል።

ይሁን እንጂ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጩኸትና ለቅሶ ምላሽ ለመስጠት ታግሎ ለማታገል በሀገር ውስጥም ሆነ  ከሀገር ውጪ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በተለያዩ የፖለቲካድርጅቶች

ሥር መሰባሰብ ከጀመሩ ቆይተዋል፡፡ ነገር ግን አብዛኞቹ የመረጡት የትግል ጎዳና በቂ ሆኖ ስላልተገኘ የብዙዎቹ ድርጅቶች አባላት ለከፍተኛ ጥቃት ተጋልጠዋል፡፡

ነገር ግን ኢብአግ የኢትዮጵያዊያንን ታሪክና ዛሬም ሆነ ለመጪው ትውልድ መብቱን አስከባሪ የሆነ አቋም በመመስረት ትግሉን በፍጥነት በማካሄድ ላይ ሲገኝ ወያኔ የሚፈጸመው በደልና ሴራን ለማክሸፍና ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማዳን የሚያስፈልገውን የትግል እርምጃ ለመውሰድ ተነስቷል፡፡

ውርደትንና ሽንገላን የመቀበል ልምድ የሌለን እኛ ልጆቿ እንደ አባቶቻችን እምቢኝ ለሐገሬ÷ ለአንድነቴ÷ ለታሪካዊ ቅርሴና ውርሴ እና ለሰንደቅ ዓላማዬ በማለት የማይታጠፍ ቃል ኪዳን ገብተን በነፍጥ እብሪት የተወጠረውን የወያኔን አገዛዝ እናንበረክከዋለን፡፡

ይህንን መሠረት በማድረግ ለዚህ ክቡርና ወቅታዊ ዓላማ ዕውን መሆን እስከ ዛሬ በኅቡዕ ስንደራጅና የትግል ስትራቴጂያችንን ስንነድፍ ከቆየን በኋላ ዛሬ በወያኔ የጎሳ ፖለቲካና አገዛዝ ላይ ሁለገብ የሆነ ትግል ለማድረግ ተነስተናል፡፡

እነሆ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር (ኢ.ብአግ) የተመሰረተበትን የፖለቲካ ፕሮግራም ለውድ ወገኖቹ በትህትና ያቀርባል፡፡

ኢትዮጵያ በሰላምና በብልፅግና ለዘላለም ትኑር!

የአብአግ የፖለቲካ የበላይ ጽ/ቤት

## ክፍል 1፤ የፖለቲካ ዓላማ

1. በኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ ድጋፍና ተሳትፎ በሚደረግ ቁርጠኛ ትግል ሃገሪቷንና ሕዝቡን አደጋ ላይ የጣለውን የወያኔ የጭቆና አገዛዝ በአፋጣኝ ከሥልጣን ማስወገድ።
2. የኢትዮጵያን የየብስ የባሕርና የአየር ብሔራዊ ክልልና ሉዓላዊነት መጠበቅ።
3. ሃገሪቷን ከጎሳ፥ ከሃይማኖትና ከቋንቋ ልዩነት ተፅዕኖ ነፃ ማድረግና አንድነቷንም በእኩልነትና በመከባበር ላይ መመስረት።
4. በነፃ ገበያ የኢኮኖሚ ሥርዓት ሃገሪቷ ወደተሻለ የዕድገት አቅጣጫ ለመራመድ የሚያስችላትን ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መመስረት።

## ክፍል 2፤ የፖለቲካ ስልት

1. ሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎች፥ የሃይማኖትና ያገር ሽማግሌዎች የሚሳተፉበት በኢትዮጵያ የሰላም፥ የዲሞክራሲና የብሔራዊ ዕርቅ ጉባዔ ተጠርቶ የሕዝብ ሥልጣንና ውክልና ያለው የሽግግር መንግሥት እንዲመሠረት ማድረግ።
2. በዚህ ሁሉን አቀፍ በሆነው የሽግግር መንግሥት ሃገሪቱ የምትተዳደርበትን ጊዚያዊ የሽግግር ወቅት መተዳደሪያና የወደፊቱን ቋሚ ሕገ መንግሥት የሚያረቅ ሕገ መንግሥቱንም ለሕዝበ ውሳኔ የሚያቀርብ የሕገ መንግሥት አርቃቂ ጉባዔኝ እንዲመሠረት ማድረግ።
3. በፖለቲካ ዙሪያ የሚነሱ ጥያቄዎችና ክርክሮች ሁሉ እልባት እንዲያገኙ በዳበረና በሰከነ የፖለቲካ ባህል በጠረጴዛ ዙሪያ በውይይት የሚፈቱበትን ሁኔታ ማመቻቸት።
4. በሕውሐት መሪነት በህዝቡ መካከል የተፈጠረውን መከፋፈል፥ ያለመተተማመንና ጥላቻን ፈጽሞ ማስወገድ፤

እናም በህዝቡ መካከል መረዳዳት ሰላምና ብልጽግና እንዲሰፍን ማበረታታት።

5. ለሰላምና ዲሞክራሲ በመፈቃቀድና በመከባበር ላይ ለተመሰረተ የሕዝብ እኩልነትና አንድነት፣ ለሃገር ህልውናና ሉዓላዊነት መረጋገጥ ከቆሙ የአንድነት ኃይሎች ጋር ልዩነቶችን አጥብቦ በማቻቻል በጋራ መሥራት።

## ክፍል 3፤ የፖለቲካዊ ጉዳዮች

1. በሕዝብ ሙሉ ድጋፍና ውሳኔ በሚጸድቀው ሕገ መንግሥት ውስጥ በሚደነገገው የመንግሥት ቅርጽና ይዘት መሠረት የመንግሥት ሥልጣን ባለቤት ሕዝቡ መሆኑን ያረጋገጠና ከጎሳ፣ ከሃይማኖት፣ ከፆታ፣ ከክልል፣ ወዘተ... ተፅዕኖ ነፃ የሆነ በህግ የበላይነት የሚመራ ሕዝባዊ ሥርዓት መመስረት።
2. ከጎሳ፣ ከቋንቋ፣ ከሃይማኖትና ከፆታ ጥበትና ልዩነት ነፃ የሆኑ ሕብረ ብሔራዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲደራጁና በተወካዮቻቸው አማካይነት ሰላማዊ ግልጽና ነፃ ውድድር አካሂደው የሕዝቡን የድጋፍ ድምጽ ብልጫ ያገኘው ፓርቲ መላው የኢትዮጵያን ህዝብ ማገልገል እንዲችል የሚያደርግ የብዙሃን ፓርቲ ሥርዓት ዕውን እንዲሆን ማድረግ።
3. መንግሥት የሕዝብ ጥረትና እድገት አስተባባሪ ስለሆነ ለልማት ቅልጥፍና አመችነት የሚመሠረቱ ብሔራዊ የአስተዳደር ክልሎች እንዲዋቀሩ ማድረግ።
4. የሀገሪቱ መታወቂያ የሕዝቡም የአንድነትና የኀልውናው ብሔራዊ መግለጫ ሆኖ የኖረው አረንጓዴ ብጫና ቀይ ህብረ ቀለማት ያለው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የማይለወጥና ተከብሮ የሚዘልቅ መሆኑን ማረጋገጥ።
5. የመገናኛ ብዙሃን ያላንዳች ገደብ የሙያና ሞራላዊ ግዴታቸውን በመጠበቅ መልዕክቶችን በነፃነት ኢንዲያሰራጩ ህጋዊ ዋስትና መስጠት።
6. በፈጣሪ አምላካችን መሪነት ይህች ቃልኪዳን የተገባላትን ሃገር

እንደ ቀድሞው ሁሉ ሃገርን የጋራ ኃይማኖትንም የግል በማድረግ በፍቅርና በአንድነት መኖርን ማበረታታት፡፡

## ክፍል 4፤ የኢኮኖሚ ጉዳዮች

1. የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ነፃነት የሚከበርበትና የህዝቡም የኑሮ ደረጃ የሚሻሻልበትን ፖሊሲ በመንደፍ በዚህም የሀገርና የህዝብ ሀብት በሚያሳየው ፍላጎትና አቅርቦት ሚዛን የሚንቀሳቀስ የነጻ ገበያ ሥርዓት የሚጠናከርበትና በውድድር ልማትና ዕድገት የሚፋጠንበትን ሥርዓት መዘርጋት፡፡
2. መንግሥት በጥናትና ምርምር ግኝቶች ላይ ተመሥርቶ ሀገሪቱ ራሷን የመመገብ አቅም እንዲኖራትና ህዝቡ በሥራ ተሰማርቶ የኑሮ ደረጃውን የሚያሻሽልበትን ጠቋሚ ዕቅድ መመስረት፡፡ በግልም ሆነ በጋራ ተቋማት የምርት የንግድና የአገልግሎት ተግባራትን ለሚያከናውኑ የኢኮኖሚ ኃይሎች አቅም የፈቀደውን ድጋፍና አገልግሎት መስጠትና ማበረታታት፡፡
3. ለሀገሪቱ ብሔራዊ ጥቅም የሚሰጠው የቅድሚያ ትኩረት እንደተጠበቀ ሆኖ በማናቸውም የኢኮኖሚ መስክ ለልማት ቅድሚያ ፈቃድና ድጋፍ የሚሰጠው ለሀገሪቱ ዜጎች ይሆናል፡፡ የውጪ ባለ መዋዕለ ንዋይ ወገኖችም በኢኮኖሚው መስክ ለራሳቸው ጥቅምና ለኢትዮጵያ ህዝብ ብልጽግና ይሰሩ ዘንድ በግልም ሆነ በማህበር ወይንም በሽርክና እንዲሳተፉ መጋበዝና ማበረታታት፡፡
4. መሬት የኢትዮጵያ ህዝብ የተፈጥሮ ጸጋና የጋራ ሀብት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለገበሬው ያለአድሎና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ በማከፋፈል ማንኛውም ዜጋ በህጋዊ መንገድ በባለቤትነት የያዘውን የገጠር መሬት ወይም የከተማ ቦታ የራሱ የማድረግ የመሸጥ የመለወጥ ወይም የማከራየት የማውረስና የማስተላለፍ መብቱ የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

5. በማንኛውም ተቋም ውስጥ የሚገኙ ሠራተኞች ተደራጅተው ከአሠሪዎቻቸው ጋር በሚያደርጉት የህብረት ስምምነት መብታቸውን እንዲያስከብሩ መንግሥት ከአሠሪዎች ጋር ተባብሮ ለሠራተኞች የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራሞች እንዲዘጋጁ የሠራተኛውን ምርታማነት የሚያሳድጉ ማበረታቻዎች እንዲሰጡ ማድረግ፤ የሥራ ቦታዎች የሠራተኛውን ጤንነትና ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ መሆናቸውን መቆጣጠርና የሠራተኞችን መሠረታዊ ፍላጎቶች ማሟላት የሚያስችልና ከገበያው ሁኔታ ጋር ተዛምዶ ያለው መነሻ ደመወዝ ከአሰሪዎችና ከሠራተኞች ጋር በመመካከር በህግ እንዲወሰን ማድረግ። እንዲሁም የዓለም የሥራ ድርጅት ስለ አሰሪዎችና ሠራተኞች ያወጣቸው ድንጋጌዎችና ውሳኔዎች ከአገሪቱ አቅም አንፃር ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ።
6. የዘላኑ ህብረተሰብ የኑሮ ደረጃቸውን ማሻሻል እንዲችሉ የእንስሳት ሀብት አያያዝና አጠቃቀም ዘዴ በማስተማር በቋሚነትም ሊሰፍሩ እንደሚችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት።
7. በልማት ወደኋላ የቀሩ አካባቢዎችንም ድጋፍ በመስጠት ዕድገታቸውን ማፋጠን፤ ለዚህም የሚሆን የተመጣጠነ የልማትና የዕድገት መርሀ ግብርን መዘርጋት።
8. ለሀገሪቱ ዕድገት እንቅፋት የሆነውን ሙስናን ለማስወገድ ጠንካራ የቁጥጥርና የክትትል ስልት መንደፍና በሥራ ላይ ማዋል።

## ክፍል 5፤ ማህበራዊ ጉዳዮች

### 5.1 ትምህርት

1. ኢትዮጵያ ማደግና መበልጸግ የምትችለው በተማረ የሰው ኃይል ዓይነትና መጠን ስለሆነ ለትምህርትና ሥልጠና ልዩ ትኩረት በማድረግ የቀለምና የሙያ ት/ቤቶች ስርጭት እንዲስፋፉ የህፃናት መዋያዎች በብዛት እንዲቋቋሙ ሥርዓተ ትምህርቱም ከኢትዮጵያ የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ጋር

እንዲሁም ከዓለም ዓቀፍ የትምህርት ዕድገት ደረጃ ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን ማድረግ፡፡

2. ተማሪዎች ሀገራቸውን ይበልጥ እንዲያውቁና በሀገር ፍቅር ስሜት ታንጸው እንዲያድጉ የሚያስችሉ ፕሮግራሞች እንዲካሄዱ ማድረግ፡፡
3. ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሀገሪቱ ዕድገትና የህዝቡ አቅም እስከፈቀደ ድረስ መደበኛና ከፍተኛ ትምህርት በነፃ የሚያገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡
4. ትምህርት ቤቶች እንዲስፋፉ እገዛ ማድረግ፡፡ የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋሞች በዓይነትም ሆነ በጥራት በማስፋፋት ብቃት ያላቸውን መምህራን ማፍራት፡፡ ለመምህራንም በሥራ ላይ ሥልጠናና ሌሎችንም ማበረታቻዎች እንዲሰጡ ማድረግ፡፡
5. የትምህርት መስጫ መሣሪያዎችን ማሟላት መሃይምነትን በህብረት ለማጥፋት መጣር፡፡

## 5.2፤ ጤና

1. የኢትዮጵያ ህዝብ የተሟላ የጤና አገልግሎት ያገኝ ዘንድ በሽታውን ለመከላከል የመሠረተ ጤና አገልግሎት ቅርንጫፎችን በሃገሪቱ መንደሮች ሁሉ ተዘርግተው ህዝቡ የጤና ጥበቃ ትምህርት እንዲያገኝ መታገል፡፡
2. ሊጠፉ የሚችሉ ተላላፊና መድኃኒት ያልተገኘላቸው እንደ ኤች አይ ቪ ኤድስ (HIV-AIDS) ያሉ በሽታዎችን በተቀናጀ አሰራር ማስወገድ የሚያስችል ብሔራዊ ዕቅድ ማውጣት፡፡
3. ዘመናዊ የህክምና መስጫ ተቋማት እንዲስፋፉ የህክምና መሳሪያዎች የመድኃኒት ምርትና አቅርቦት ልዩ ትኩረት እንዲሰጣቸው የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ በጤናው ዘርፍ የሚኖረውን ተሳትፎና ሚና ማሳደግ፡፡
4. ጠቃሚነታቸው ተጠንቶ የተረጋገጠላቸው የባህል መድኃኒቶች በጥረት እንዲዘጋጁና እንዲሰራጩ ማገዝ፤
5. የጤና አገልግሎቶች ስርጭት ሚዛናዊ እንዲሆን ልዩ ጥረት ማድረግ፡፡

6. ለህዝቡ ንፁህ የመጠጥ ውሃ አገልግሎትን ማዳረስ፡፡

## 5.3፤ ሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች

1. የሀገሪቱ የምርት፥ የንግድና የአገልግሎት ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች የሀገሪቱን ዜጎች ሥራ የማግኘት ዕድል የሚያስፋፋ የአሠራር ስልት እንዲከተሉ ኢትዮጵያዊያን በሀገራቸው ውስጥም ሆነ ከሀገራቸው ውጪ ሥራ ፈልገው ለመያዝ ያላቸው መብት ያለገደብ እንዲረጋገጥና ለሥራ ስምሪት የሚረዱ የአጭርና የረዥም ጊዜ የሙያ ስልጠና ፕሮግራሞች እንዲስፋፉ ልዩ ትኩረት መስጠት፡፡
2. የአገልግሎት ዘመናቸውን አጠናቀው በጡረታ ለሚገለሉ ወይም በሀገር መከላከል አካላቸውን ላጡ ጀግኖች የሚከፈለው አበል በየወቅቱ ከሚኖረው የገበያ ዋጋ አንፃር እየታየ እንዲስተካከልና ሌሎች የመተዳደሪያ ዋስትናዎች እየተጠኑ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡
3. ከራሳቸው ቁጥጥር ውጪ በሆኑ ምክንያቶች በዝሙት አዳሪነትና በልመና ተግባራት ላይ የተሰማሩ ዜጎች ለራሳቸውና ለህብረተሰቡም በሚጠቅሙ ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ፡፡
4. ለወጣት አጥፊዎች ተሐድሶ ልዩ ትኩረት እንዲሰጥና በአካላቸው መጉደል በዕድሜያቸው ማነስ ወይም መግፋት ምክንያት ሠርተው መተዳደር ለማይችሉና ደጋፊ ለሌላቸው ህብረተሰቡ በተቀናጀ መንገድ የሚረዳበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡
5. በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋዎች የሚጎዱ ዜጎችን ችግር ለዘለቄታው ለማስወገድ የተቀላጠፈ ፈጥኖ ደራሽ እርዳታ መስጠት፡፡
6. በወያኔ ሴራና ደባ ምክንያት ወደ ጎረቤትና ሌሎችም ሀገሮች በመሰደድ ችግር ላይ የሚገኙትን ዜጎች ከተባበሩት መንግሥታትና አግባብ ካላቸው ሌሎች መንግሥታት ጋር ተባብሮ ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ ከወገኖቻቸው ጋር ተዋህደው መደበኛ ኑሯቸውን የሚመሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

7. የሀገሪቱን ባህል ለመጠበቅ ሰዓሊዎች፥ ደራስያን፥ ሙዚቀኞች፥ ድምፃዊያን፥ ተዋንያን እና ሌሎች የሥነ-ጥበብ ባለሞያተኞች ሙያቸውን ይበልጥ ያዳብሩ ዘንድ እገዛ እንዲደረግላቸው ታሪካዊ የሃይማኖትና የባህል ቅርሶች በጥንቃቄ እንዲጠበቁ እንዲሁም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች፥ ልማዶች፥ ወጎችና ወዘተ... በብሔራዊ ደረጃ አንድ ማዕከል ተቋቋሞ ጥልቅ ጥናትና ምርምር እንዲካሔድ አጥብቆ መታገል፡፡

## 5.4፧ ሃይማኖት

1. መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ መሆናቸውን በማረጋገጥ የሕዝቡን ነጻነት መጠበቅ፡፡
2. በሀገሪቷ ሁሉ የሃይማኖትና የዕምነት እኩልነት የተከበረ ማድረግ፡፡
3. በሃይማኖት ሽፋን የሃገሪቷን ብሔራዊ ጥቅም ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት የሚፃረር ማናቸውንም አደገኛ እንቅስቃሴዎች በቅርብ መከታተል፡፡

## 5.5፧ ቋንቋ

1. ኢትዮጵያ የበርካታ ቋንቋዎችና ባህሎች ባለቤት መሆኗ ሌሎችን የሚያስቀናና አገሪቱን የሚያስከብራት በመሆኑ በተለያዩ ታሪካዊ ምክንያቶችና አጋጣሚዎች የዳበሩ ቋንቋዎችና ባህሎች ብሔረሰባዊና አካባቢያዊ መለዮ እየተሰጣቸው ከሚወገዙ ይልቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ የወል ግኝቶች መሆናቸው ታውቆ እንድንጠቀምባቸውና እንድንጠብቃቸው ልዩ ትኩረት መስጠት፡፡
2. የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ቋንቋ እንዲያድግና እንዲጠበቅ ልዩ ትኩረት መስጠት፡፡
3. የእያንዳንዱ ብሔረሰብ ቋንቋ ዕኩልነት ተጠብቆ ይበልጥ እንዲዳብር ሊደረግለት የሚገባው እገዛ እንደተጠበቀ ሆኖ ከነዚህ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች መካከል አንዱ ብሔራዊ ቋንቋ ሆኖ ያገለግል ዘንድ በህዝበ ውሳኔ እንዲመረጥና የሀገሪቱ

የጋራ መግባቢያ ቋንቋ እንዲሆን ማስተባበርና ማረጋገጥ።

## ክፍል 6፤ የዜጎች መሠረታዊ መብቶች

1. የዜጎች የመሥራት፥ የመናገር፥ የመፃፍ፥ የመደራጀት፥ ሃሳብን በሰላማዊ ሰልፍ የመግለፅ፥ የመሰብሰብ፥ ሥራ የማቆም እና የመረጡትን ፍላጎት የማራመድ መብት ማስከበር።
2. የአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን ቻርተሮችን ማክበር።
3. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በአገሩ ውስጥ በማንኛውም ክልል ያለገደብ በነፃነት የመዘዋወር የመኖር የመሥራትና ሀብት የማፍራት ማህበራዊ ኑሮውን በዕኩልነት የማራመድ መብቱ እንዲከበር ማድረግ።
4. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አግባብ ካለው ህጋዊ አካል ትዕዛዝና ውሳኔ ውጪ የዜግነት መብቱን እንዳያጣ፤ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር እንዳይታሰር፤ የመኖሪያና የሥራ ቦታውም ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዳይፈተሽ ማድረግ።
5. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የግል ይዞታ ሀብቱን የመሸጥ የመለወጥና የማውረስ መብቱና የንብረት ባለቤትነቱ እንዲከበር ማድረግ።
6. እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ዕድሜው ለአካለ መጠን ሲደርስ በአዕምሮ ህመምና በፍርድ ቤት ውሳኔ ካልሆነ በስተቀር በሀገሪቱ የፖለቲካ ሥርዓት ሂደት ውስጥ የመሳተፍ የመምረጥና የመመረጥ መብቱ እንዲከበር ማድረግ።

# ክፍል 7፤ የሀገር መከላከያ፥ የፖሊስና የብሔራዊ ደህንነት አደረጃጀት

## 7.1፤ የሀገር መከላከያ

1. የኢትዮጵያ ዳር ድንበር የህዝቧን ሰላምና አንድነት ሉዓላዊነት ነፃነትና ሰንደቅ ዓላማዋን የሚያስከብር ፅኑዕ የሆነና ከሁሉም የኢትዮጵያ ልጆች መካከል በሙያቸው በዝንባሌያቸው በብቃታቸውና በፍላጎታቸው የሚመለመል ብሔራዊ የሀገር መከላከያ ሠራዊት እንዲቋቋም መጣር።
2. የሚቋቋመው ሠራዊት ከፖለቲካ ሥልጣን ውድድር ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲዎች ከጎሳና ከሃይማኖት ተፅዕኖና ግፊት ነፃ የሆነ በህዝብ መብትና የፖለቲካ ጥያቄ ጣልቃ የማይገባ በሀገሪቱ ህገ-መንግሥት ውሳኔና ትዕዛዝ የሚመራ ብሔራዊ የሀገር መከላከያ ሠራዊት እንዲሆን ማድረግ።
3. ከቀድሞው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባላት በብቃታቸው በዕድሜያቸውና በፈቃደኝነታቸው ላይ ተመስርቶ የሚሳተፉበት የኢትዮጵያ ሀገራዊ አንድነትና ነፃነት የሚረጋገጥበት በዘመናዊ ወታደራዊ ሙያ የሰለጠነ ጠንካራ የመከላከያ ኃይል መገንባት።

## 7.2፤ ፖሊስና ደህንነት

1. የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅሞች የሕዝቧን ደህንነትና ሰላም ህግና ፍትኅ ለማስከበር ሙያዊ ጥራትና ብቃት ያለው ብሔራዊ የፖሊስና የደኅንነት ኃይል ማቋቋም።
2. የፖሊስና የደህንነት ኃይል ብሔረሰባዊ ስብጥር ከሁሉም የአገሪቱ ልጆች የተውጣጣ እንዲሆን ማድረግ።
3. የሚቋቋመው የፖሊስና የደኅንነት ኃይል ከማናቸውም የፖለቲካ ተሳትፎ በህግ የታገደ ማድረግ።

## ክፍል 8፤ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ

1. ከማናቸውም የውጪ መንግሥታት ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ ብሔራዊ ጥቅምን የሚያስከብር ከማናቸውም ሀገርና መንግሥት በመከባበር በዕኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ በተመሠረተ ተባብሮ መሥራት የሚያስችል የውጭ ፖሊሲ መንደፍ።
2. የኢትዮጵያ የውጪ ፖሊሲ ኢኮኖሚያዊ ማኅበራዊ ባኅላዊና ቴክኖሎጂያዊ ዕድገትን ለማፋጠን የሚያግዝ በሌሎች ሀገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ባለመግባት መከባበርና መተሳሰብን ሰላምን ትብብርንና የጋራ ዕድገትን የሚያጠናክር እንዲሆን መታገል።
3. ለዓለም ሰላምና ዲሞክራሲ ከሚታገሉ ኃይሎች ጎን በመሰለፍ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ማስከበርና በዓለም ፊት ስለኢትዮጵያ የተፈጠረውን የተዛባ አመለካከት ለውጦ ሀገሪቱንና ህዝቧን የሚያስከብር እንዲሆን መጣር።
4. የኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ብሔራዊ ጥቅምን እስካልተጋፋ ድረስ የተባበሩት መንግሥታትና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲሁም የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች ቻርተሮችን ማክበር።
5. የኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት የተከበረና የማይደፈር እንዲሆንና ህጋዊ የወደብ ባለቤትነቷን ለማረጋገጥ ዲፕሎማሲያዊ ትግል ማድረግ። በዚህ ረገድ ወያኔ/ኢሕአዲግ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የተዋዋላቸው ውሎች ህጋዊ መሠረት የሌላቸውና ውድቅ መሆናቸውን ማረጋገጥ።

**<u>አድራሻ</u>**

**የአብአግ የፖለቲካ የበላይ ጽ/ቤት**

**የመልዕክት ሣጥን ቁጥር** 00000

**ክሌርሞንት፥ ካሊፎርንያ** 9----

**ሰሜን አሜሪካ**

**<u>የፋክስ ቁጥር</u>**

(000) 000-0000